# በአንድ ፍላፃ ሶስት ጫፎች ፡-ምስክርነት ከወንጀለኞች አንደበት?

## (የመጨረሻ ክፍል)

በህያዉ ቃል

የ"ምስክርነት" ጸሃፊ ፡ በአንድ የታሪካችን ወቅት ላይ ባለፈዉ የሽብር -የጽልመት ዘመን ዉስጥ በብሔራዊ ደረጃ ስለተፈጸመዉ ጥፋት የሥርዓቱን መሓንዲሶች ከዘንጣይ ገዳዮቻቸዉ ጋር አሰልፈዉ ማስረጃ አቀረብኩላችሁ ይሉናል።አልታወቃቸዉ ይሆናል ።እንጂማ የየካቲቱን አብዮት ተከትሎ በመላይቱ ኢትዮጵያ ስለታየዉ ክስተት በገለፁባቸዉ የድርሰቱ ክፍሎች ሁሉ ገጽ በገጽ "ዛሬም ነገም -ቀይ ሽብር ይፋፋም / "የሚል የቀድሞ መፈክራቸዉን ያስተጋባሉ፡-በለሆሳስ -ለአንባቢዉ ።በዚህ መሰል ደፋርነትም በታሪካችን ላይ ይዘምታሉ። ለፍትህና ለነጻነት በተደረገዉ ትግል ዉስጥ በአገርና በወገን ፍቅር ነድደዉ አካላቸዉንና ሕይወታቸዉን ቤዛ አድርገዉ ያለፉትን ሰማዕት አንጸባራቂ ገድል ያኮስሳሉ ። በዚህም ብቻ አይቆጠቡም ። በሞራላችን ፡ በአመክኖአዊዉ አስተሳሰባችንና ግንዛቤአችን ላይ ሁለገብ ጦርነት ያወጁ በሚያስመስላቸዉ ድምጸት ያሾፋሉ ፡ (ሹፈት እንበለዉ እንጂ- ቢያንስ ወደርሳቸዉ አዘቅት ላለመዉረድ ) ለማገናዘቢያ ያህል በሮማዉያኑ ቁጥር ገጽ 7 ላይ ያሰፈሩትን እንመልከት ።

> ቀይ ሽማ የለበሰዉ ኢሕአፓ (ሁኔታዉ ሲያጥጥ አብዛኛዎቹ የኢህአፓ መሪዎች
>
> ከጡት እናታቸዉ አሜሪካ ነዉ የገቡት ። እዉነት ኮሙኒስት ቢሆኑማ (ኖሮ? ) እንዲያ
>
> አምርረዉ ከሚጠሉት ደም መጣጭ ካፒታሊስት አገር ያዉም አሜሪካ / እንዴት
>
> ይሔዱ ነበር?? ትክል ስለነበሩ ምዕራብ ገብተዋል ።

ልብ በሉ ። መርማሪዉ ሻምበል (የአንድ የማዕከላዊ ምርመራ ሻምበል የሥራ ዝርዝርና ሓላፊነት ከየት እስከ ዬት እንደሆነ ባይነግሩንም የየራሳችን ግምት ይኖረናል ፡) ለመሾሚያ መሸለሚያቸዉ ሲሉ አረመኔነታቸዉን ለማስመስከር የፈጸሙት ግፍ የተዋለበትን ያን ትዉልድ ዛሬም ይዘባበቱበታል ። ርሳቸዉን የመሳሰሉ ቅጥረኞችና ፋሽስት አዝማቾቻቸዉ በሥልጣን ሰክረዉና በሕዝብ ልጆች ስቃይና ሞት መርቅነዉ በሚፍነሸነሹበት በዚያ የእብሪት የእብደት ዘመናቸዉ በተዐምር ተርፈዉ በሕይወት ሊያመልጡ (ያዉም በስደት) የታደሉትን ጥቂት ወገኖች ዛሬም አይምሯቸዉም ። ያሰፈሩትም ሃሳብ ቢሆን የድርጅቱን ርዕዮተዐለማዊ ወገንተኝነት ለማጋለጥ ብለዉ ያቀናበሩት ከመምሰል ይልቅ "ለምን አመለጡኝ ??" ከሚል የሰዉ ስቃይ ናፋቂነት የመነጨ ነዉ የሚመስለዉ ። እርግጥ ነዉ ባሁኑ ወቅት ሻምበሉ እነዚህን ከሞት ያመለጡ ኢትዮጵያዉያን/ያት በአካል አይደርሱባቸዉም ። በፈንታዉ ዉሃ በማያነሳ የነገር ጨፈቃ ሊሸነቁጧቸዉ ነዉ የሚቃጡት ።

ተወልዶ ባደገበት አገር ደም የሚያነፈንፉ የቀን ጅቦች እያሳደዱ መድረሻ ያሳጡት ሰዉ(ዎች ) ዬትስ ቢሆን እጁን ዘርግቶ ወደሚቀበል ወገንና ቀዬ መግባቱ(ታቸዉ ) ተፈጥሮአዊ አይደለምን???ሻምበሌ ልጠይቅዎ ፡ ለመሆኑ ወያኔ አዲስ አበባ የገባ ሰሞን የደርጉ ዱታ ነኝ ባይ ሃምሳ አለቃ ለገሰ አስፋዉ ዬትና

እንዴት ነበር የተያዙት?? በአንድ ገጠር ዉስጥ እንጨት ተሸክመዉ አህያ በመንዳት ላይ ሳሉ ነበር የሚባለዉ እዉነት ነዉ?? ከሆነ መቼም እዚያ ድረስ ዘልቀዉ የገቡት የገበሬዎች አምራቾች ማሕበር ለማቋቋም ነበር የሚል ደፋር እንደማይገኝ ርግጠኛ ነኝ ። ጸሓፊዉ ገጽ 24 ላይ እንደሚያስነብቡን የጎንደሩ አራጅ መላኩ ተፈራና በጋሻዉ አታላይ ከአገር ጠፍተዉ ከወጡ በሁዋላ ጂቡቲ ዉስጥ ነበር ተይዘዉ የተመለሱት ። ለምን ብሎ ለጠየቀ መልሱ ከፈረንሳዮች ወይም ከአፋርና ኢሳዎች ጋር የርዕዮተ ዐለም ወይም የጋብቻ ትስስር ስለነበራቸዉ ነዉ ይሆናልን??? ለመሆኑ ሻምበል ተስፋዬ ራስዎ ወያኔ በዘር ማጥፋት ወንጀል ያከናነበዎትን ከአንድ አሥርት በላይ የዘለቀ የእስር ቤት ኑሮ ከፈጸሙ በሁዋላ ዬት ነዉ የሚኖሩት?? --ብቻ ከምዕራብ አገሮች በአንዱ እንዳይሆን ።መቼም ርስዎን የመሰለ "የስታሊን -በትረኛ" የስደት ፌርማታዉን ሩስያ አልያም ኩባ ነዉ ማድረግ ያለበት ። (አይቆጡ፡ለሌላዉ የቀጠፉት አርጩሜ ማሳመሙ በይበልጥ የሚታወቀዉ ሲገረፉበት ነዉ ። )

ሌላዉ እጅጉኑ ጎልቶ የሚታየዉ አስተዛዛቢ ነገር ሻምበል ተስፋዬ ዋቢ የሚያሳልፏቸዉ ሰነዶች ጉዳይ ነዉ ።እማኝ አድርገዉ የሚያሰፍሯቸዉ ሰነዶች የሚኖራቸዉን ተአማኒነት ከቁብ አያስገቡትም ። ብቻ ደርግንና ኢ-ሰብአዊ አገዛዙን ከኩነኔ የሚያርቅላቸዉ ሆኖ ይገኝ እንጂ ስለተገቢነት ዋጋዉ ከቶ አይጨነቁም ።ለአብነት ያህል በሮማዉያኑ ቁጥር ገጽ9 ላይ ያሰፈሩትን እንመልከት ። " ደርግ በሁለት ጎራ ተሰልፈዉ በተፋለሙ ምሁራን ግፊት " ሳይወድ በግድ ተጎትቶ ገባ እንጂ "ቀይ-ሽብርን "እስከነቋንቋዉም አያዉቀዉ እንደነበር ይደመድሙልናል ። ለዚህ ድምዳሜአቸዉ በማመሳከሪያነት የሚጠቅሱት ሰነድ ግን ቁንጮዉ የደርግ ባለሥልጣን ፍስሓ ደስታ በየካቲት 1997 ለተከሰሱበት አንደኛ የወንጀል ችሎት የሰጡት የመከላከያ መልስ ነዉ ። እዚህ ላይ ሻምበሉ በአጽንዖት የሚያሰምሩበት ጉዳይ በወቅቱ መኢሶንና ኢሕአፓ መስመር ለይተዉ ባደረጉት ትግል ዉስጥ ደርግንና አገዛዙን በመሣሪያነት የተገለገሉበት መሆኑን ነዉ ።በዚህ አተያይ የደርግ ሚና ከግዑዝ መጠቀሚያነት ያላለፈ ፡ ለተከተለዉ ጥፋትም በሃላፊነት የማይጠየቅበት ነዉ ። ለርሳቸዉ ጠመንጃ ነዉ ። ተተኮሰ - ሰዎች ሞቱ ። ተኩዋሾቹ ግን ምሁራኑ - መኢሶንና ኢሕአፓ ነበሩ ነዉ የሚሉን ። በዚህ መከራከሪያቸዉ ዉስጥ ቃዬልም አቤልም እኩል የጅምላ ዉሳኔአቸዉ ፍርደኛ ሆነዉ ይቀርባሉ። "የሕሊና ፍርድ ደህና ሰንብች " ማለትስ ይኼኔ ነዉ።

እዉነት ነዉ ፡ ለሥርዐት ለዉጥ በተደረገዉ ሕዝባዊ እንቅስቃሴ ዉስጥ ኢሕአፓ የተከተለዉ የትግል መስመር የነደፋቸዉ መርሐ ግብሮችና ያራመዳቸዉ ፖሊሲዎች ወታደራዊዉ ደርግም ዉስጥ ሥርፀዉ የመግባት ብርታት የነበራቸዉ ነበሩ ።ቁጥራቸዉ አነስተኛም ቢሆን በወቅቱ ተደማጭነት የነበራቸዉ የደርግ አባላት የኢሕአፓን መርህ በመደገፍ የደርግን አካሄድ ለማስተካከልና በማቆጥቆጥ ላይ የነበረዉን አምባገነናዊ አዝማሚያዉን ለማረቅ በጎ ጥረት አድርገዋል። በዚህ መሰሉ የዉስጥ ትግል ላይ ሳሉ የኮሎኔሉ ቡድነኞች "ቁርስ " ያደረጉአቸዉ የደርግ አባላት መኖራቸዉ አይዘነጋም ። ኢሕአፓ በጊዜዉ ደርግን ይዘዉረዉ ነበር ለማለት የማይቦዝኑት ተስፋዬና መሰሎቻቸዉ መዘወሪያዉ ድርጅቱና አባላቱ የነበራቸዉ በሳል አስተሳሰብና የኢትዮጵያን መፃዒ ዕድል አስመልክቶ የነበራቸዉ አመለካከት ትክክለኛነት መሆኑን ግን መቀበል ይቸገራሉ ። በዚያ ወቅት አብሮ መሥራት በሚል ዘይቤ ከደርግ ብብት በመመሰግ ከዉስጥ መዘወርን የትኛዉ ወገን ስትራቴጂዉ አድርጎ ሲንቀሳቀስ እንደቆዬማ ከልሂቅ እስከ ደቂቅ ያዉቀዋል ። ሻምበል ተስፋዬ የአዉራዬቱን መኢሶን ; የዶ/ር ንግሥት አዳነን " አስተምረን አስተምረን / መንግሥቱ ሀይለማርያም ከዳን ። " የቁጭት አባባል ደጋግመዉ ጠቅሰዉታል ። በትርጓሜዉ ግን በዚያ የግፍ ዘመን ማን ማንን ሲሾፍር እንደነበር ትክክለኛዉን ሳያመላክታቸዉ መቅረቱ እጅጉኑ የሚያስደምም ሆኖ አግኝቼዋለሁ ። ዳሩ "አዉቆ የተኛ ቢጠሩት አይሰማም ። የ "ምስክርነት "

ጸሀፊ የጭካኔአቸዉ ደረጃ  በሰዉ ዐዕምሮ ሊታሰብ ከሚችለዉ በላይ ከነበሩት የስቃይ ጠቢባን አንዱ የነበረዉን  ተኮላ ማሞን  "ታዋቂዉና  አስጨናቂዉ መርማሪ "  የሚል ቅጽል ደርበዉለት ሲያሞካሹት (ገጽ  105 ) የእምነታቸዉን ገመና ፀሀይ አስመትተዉታል ።

ይህንን  ጉዳይ በሚመለከት ፡ ሳያዉቁት ቀርቶ ; ወይም ዐዕምሮአቸዉና ብዕራቸዉ የማይናበቡ ሆኖ ከዚያ ሁሉ ጥራዝ ጽሁፋቸዉ ሁሉ  የደሕንነቱን መ/ ቤት ቁንጮ የተስፋዬ  ወልደ ሥላሴን አስተያየት የደመደሙበት አንቀጽ (ገጽ 90 )ሚዛን የሚደፋና ትዝብት ላይ የሚጥላቸዉን  እዉነት አዝሏልና መጠቀስ ይኖርበታል ። "በወጣቱ ላይ  ዕልቂት ያደረሱ መኢሶኖች ናቸዉ ። የሚችሉትን ገደሉ ፡ ያልቻሉትን እየጠቆሙ አስገደሉ ። ያሜሩት  መኢሶን ፡ ወዝ- ሊግ ፡ የመንግሥቱ ተከታይ  የደርግ አባላት ናቸዉ ።" ጠቅለል ባለ አነጋገር ፡ይህንን መራር ግን ገናን እዉነት ነዉ ላያመልጡ  የሚሸሹት - ጸሀፊዉ መርማሪ ሻምበል  ።

ሽብር በሕግ በተደነገገበትና  መንግሥታዊ ተግባር ተደርጎ በተወሰደበት  በዚያ የጽልመት ዘመን ለኢትዮጵያና ለሕዝቧ ታላቅ ፍቅር ፡ ፍትህ እኩልነትና ዴሞክራሲ ለሰፈነበት ሕብረተሰብ ዉጥን ህልም የነበራቸዉ አያሌዎች በትግል ላይ ሆነዉ ግንባራቸዉን ሳያጥፉ ተሰዉተዋል - ታስረዋል - ተሰደዋል ። የአካላዊ ሥቃይን ጠባሣና  ሰንበር በገላዎቻቸዉ ላይ እስከዛሬ  አገልድመዉ የሚኖሩትም ወገኖቻችን የዚያኑ ያህል ከፍተኛ ቁጥር ያላቸዉ  ናቸዉ ። በግብግቡ  ዉስጥ የሕዝብን ቀልብ የሳበዉና በተለይም የወጣቱን ትዉልድ ልቡና ከዐዕምሮ የማረከዉ  ኢሕአፓ  እንደ ፖለቲካ ድርጅት የከፈለዉ ዋጋ ግዙፍ ፡ የደረሰበትም ጉዳት ከፍተኛ ነዉ ። ይህንን እዉነታ ፡ ይህንን ታሪክ ነዉ እንግዲህ ፡ እነተስፋዬ የግልብጥ ጽፈዉ ሊያስነብቡን የሚቃጣቸዉ ። ሆነ ብለዉ ፡ በሃገር ላይ የጥፋት እጃቸዉን ካነሱት ሀይሎች ዝርዝር ዉስጥ  ኢሕአፓን ይቀይጡታል ።ለዚህም  ማመላከቻ  እንዲሆናቸዉ  በወቅቱ  ከኢሕአፓ በመክዳት ከአሸባሪዎቹ ሀይሎች ጋር የተቀላቀሉትን  "አንጃ "ዎች  አሳፋሪ ግብር ምሳሌ አድርገዉ ይጠቅሳሉ ። የአንጃዉ አባላት በቀድሞዉ ድርጅታቸዉ ህልዉናና  በጉዋዶቻቸዉ  ሕይወት ላይ ላደረጉት የጥፋት ዘመቻና በትዉልድ ላይ ለደረሰዉ እልቂት የተጠያቂነት ድርሻ የሚኖርባቸዉ መሆኑን ማንም አይስተዉም ። ሆኖም እነዚህ ወዶ-ገቦች  "ኢሕአፓ " የሚለዉን በተለምዶ ለድርጅቱ አባላትም የሚሰጠዉን መጠሪያ በክህደት ድርጅቱን ጥለዉ የወጡ ቀን ከላያቸዉ ላይ ገፍፈዉ የጣሉት መሆኑን  እነሻምበል ጸሃፊ ልብ ሊሉት ይገባል ። አንድ ካህን ካፈረሰ  በሁዋላ ዳግም  "ቄስ "ተብሎ አይጠራም ፡- አንጃም እንደዚያዉ ነዉ።

በመጨረሻም ፡ በቅርብ ጊዜዉ የአገራችን ታሪክ በተከሰቱት አሳዛኝ ሁኔታዎች ዉስጥ ከአፍራሽ ሀይሎች ጋር ተሰልፈዉ የተንቦጨቁቱ ወገኖች ሳይቀሩ በግልና በቡድን ደረጃ ተጽዕኖአቸዉን ያሳረፉበትን የጊዜ ክልል የሚመለከቱ መጽሐፎችን እያሳተሙ ገበያ ማዉጣት መጀመራቸዉን እያስተዋልን ነዉ ። ዓላማቸዉ ከገንዘብ ማስገኛነቱ ወዲያ የተደነጋገርንባቸዉንና እስከዛሬም ድረስ  በቅጡ አጥጋቢ መልሰ ያላገኘንላቸዉን ጉዳዮች ለማጥራትና  ከአላፊዉ ስህተት የምንቀስመዉን አስተምህሮ ለማጉላት በሆነና ምንኛ ባበረታታናቸዉ ። የአብዛኛዎቹ ግብ ግን በተቃራኒዉ ሆኖ አገራዊ ዉርደትን ያከናነበንን የግፍ አገዛዝ በጥብቅና ሲያገለግሉ  ነዉ  የሚስተዋሉት ። አንባቢዉም ቢሆን የገንዘብ ቦርሳዉን ከመምዘዙ በፊት ስለሚገዛቸዉ የህትመት ዉጤቶች ፋይዳ ጥያቄ ሲያነሳ  በፍጹም አይታይም ።በዚህ አያያዝ ከተዘለቀና " ወንጀል - መጽሐፍ - ገንዘብ " ትርፍ እንደሚያስገኝ   አንድ ሂደት መታዬት ከጀመሩ  የከፋ ችግር መጋረጡ አይቀሬ ይሆናል ።

በነገራችን ላይ የደርጉ ሊቀ መንበርም ከሰሞኑ መጽሀፍ አሳትመዉ አከፋፋይ በማፈላለግ ላይ መሆናቸዉ ይሰማል ።ምን ሊነግሩን ዘይደዉ ይሆን ???? ርሳቸዉ እንደሆኑ "ትንኝ  እንኩዋን ገድለዉ አያዉቁምና " እንደጲላጦስ " ከደሙ ንጹህ ነኝ " ብለዉ እጃቸዉን ቢታጠቡ አይደንቀኝም ። የዚያኑ ያህልም በአገዛዝ ዘመናቸዉ ለደረሰዉ ዉድቀት ሁሉ ተጠያቂዉ ኢሕአፓ መሆኑን ቢምሉበት አይገርመኝም ፡- ዉሸት ለመናገር ጭካኔ አያስፈልግም ያለዉ ማነዉ ????? -- አዶልፍ ኤክማን በስተፍጻሜዉ ከገዛ ራሱ ጋር ሰላም ማዉረድ እንደሚሻ ነበር የተናገረዉ ??--- ልብ ያለዉ ልብ ይበል ።

-----------------*******________________